# ዘፋኞቻችን ሆይ! እስኪ አንዳንዴም ቁምነገር ዝፈኑልን!

እርግጥ ነው እግዚአብሔር ይመስገንና በጣም ጥቂት ቢሆኑም ቁም ነገር የሚዘፍኑ ማለትም በዘፈኖቻቸው የበቃ ተረካቢ ትውልድ እንዲፈራ የሚያንጽ መልእክት የሚያስተላልፉ፣ የሚመክሩ፣ የሚገስጹ፣ የሚያስተምሩ ዘፋኞች አሉን፡፡ ምንም እንኳ ከነዚህ ውስጥ አንዳንዶቹ አንዳንዴ ያልተገባ ሥራ ቢሠሩም ቅሉ፡፡

የሚበዙት ግን አልበሞችን (የዘፈን ጥራዞችን) አስቀርጸውም ወይም አውጥተውም አንድ እንኳ የሚነሣ ቁምነገር የሌላቸው ናቸው፡፡ ስለፍቅር አዜምን ብለው ትውልድን የሚያስት፣ ወዳልተፈለገ አቅጣጫ የሚነዳ፣ ጋጠወጥነትን የሚያበረታታ፣ ለሞራል (ለቅስም) ልሽቀት ዝቅጠት ኪሳራና ስብራት የሚዳርግ ዘፈን የሚዘፍኑ ናቸው፡፡ በእነሱ መረዳት ፍቅር ማለት ከማንም ጋር መዳራት ማለት ነው፡፡

ኃላፊነት የሚባል ነገር አይሰማቸውም፡፡ ራሱ ኃላፊነት ማለት ምን ማለት እንደሆነ የማያውቁ የማይገባቸውም ናቸው፡፡ ስሜታቸው ያዘዛቸውን ብቻ የሚሠሩ ናቸው፡፡ መስሎ እስከታያቸው ጊዜ ድረስ ማንም ምንም ቢል ምንም ዓይነት ጉዳት ቢያስከትል ግድ አይሰጣቸውም፡፡ የሚሠሯቸው ሥራዎች ትውልድን እንደማሳቱ እንደማደንቆሩ ሀገር የሚጎዳ ጥፋት ወይም የጠላት ሥራ እየሠሩ እንደሆነ ምንም የማይረዱ የማይገነዘቡ ናቸው፡፡ ማስተዋሉን ሰጥቶ ለሀገር ለወገን ለራሳቸውም የሚጠቅሙ ያድርጋቸው እንጅ ሌላ ምን ይባላል?

ይሄ ነገር ቢያሳስበኝ ከአምስት ዓመታት በፊት አንድ ዘፈን "ፋሽን" በሚል ርእስ ደረስኩና ለአቀናባሪ ከፍየ እራሴው ተጫውቸ ለብዙኃን መገናኛዎቹ እየዞርኩ አደልኩት፡፡ ይገርማቹሀል አንዳቸውም እንኳ ሊያጫውቱት አልፈለጉም፡፡ ስንት ተወዛገብን መሰላቹህ፡፡ ወቀሳየንና ስሕተታቸውን ጋዜጣ ላይ ሳይቀር ጻፍኩት፡፡ ዘፈኑን በፈለገ እናንት **(you tube)** ላይ ጭኘዋለሁ ይሄንን ይዝ (ሊንክ) ተጭናቹህ ከፈቱትና አዳምጡት፡፡

**https://www.youtube.com/watch?v=izBuMImOOy0**

ስታዳምጡት የብዙኃን መገናኛዎቹ ዘፈኑን "አናስደምጥም!" ያሉበት አንዱ ምክንያት ይገባቹሀል፡፡ ግጥሙ አልሰማ ካላቹህ አስተያየት መስጫው ላይ ስላስቀመጥኩት እዚያ ላይ ልትመለከቱት ትችላላቹህ፡፡

እስኪ ለዛሬ ከዚህ ቀደም ቁምነገር ያዜሙ ለነበሩትም ሆነ ላልነበሩት ይሄንን ስለ ሴት ልጅ የሚያነሣሣ ማኅበራዊ ግጥም እንካቹህ ብያለሁና የፈለገ በጣፋጭ ዜማ አዋዝቶ ሊያዜምልን ይችላል፡-

## እሷ

እሷ ክብርት ናት ፤ ብርቅ የአምላክ ሥራ

ድንቅ ሆና የታነጸች ፤ ከውድ ስጦታ ጋራ

እንድናገኝባት ፤ ጸጋ ሰላም ተድላ

ለፍጥረቱ ሁሉ ፤ ሆና እናት ጥላ፡፡

ሴትነት ብርቅ ድንቅ ፤ የመባረክ ዋጋ

ቢሆንም መታደል ፤ የመወደድ ጸጋ

ከባድ ኃላፊነት ፤ አለውና አደጋ

ዋ! ልቅበጥበጥ ላለ ፤ ዋ! ለተዘናጋ

ያንን የከበረ ፤ የአምላክ ስጦታ

ወስዶ ሲያጌጥበት ፤ ከአንቺ አስጥሎ በአፍታ

ሁሌም የሚያደባ ፤ በሔድሽበት ቦታ

አለና ስድ ዋልጌ ፤ ዋ! ያሸለብሽ ለታ፡፡

ይሄንን ስጦታ ፤ የከበረ ዕቃ

እንዴት እንደሚያዝ ፤ ያልገባት ያች ጮርቃ

በአጉል ጊዜ ላይ ፤ ለማንም ወንድ ሰጥታ

ስንት ፍዳ ታያለች ፤ ምስቅልቅል ውስጥ ገብታ፡፡

እናም አንቺ እኅቴ ፤ ታዳጊ የአውሬው

ተፈጥሮ የጣለብሽ ፤ ከባድ ነውና ዕዳው

ድንቅ ስጦታሽን ፤ አላግባብ ተጠቅመሽ

ውድ ዋጋ ሳትከፍይ ፤ ተጠንቀቂ እባክሽ !

በኮረዳነት ወቅት ፤ በፈጸሙት ስሕተት

ለኋለኛው ዘመን ፤ ጉዳቱን ሳያውቁት

መውለድ ተስኗቸው ፤ ካገቡ በኋላ

ስንት የሚያለቅሱ አሉ ፤ ብሎ የልብ አልሞላ፡፡

የሴት ልጅ መከራ ፤ እንዲህ ጸንቶ ዕያዬ

የማይሰማው ወንድ ፤ ካለ ልብ ድውዬ

ይሄ ሰው አይደለም ፤ እንስሳ ነው ጎጋ

ይሒድ ይቀላቀል ፤ ከአራዊቱ መንጋ፡፡

ሠዓሊ አምሳሉ ገ/ኪዳን አርጋው

amsalugkidan@gmail.com